አፍሪካ ቲቪ

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

11

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች 5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 39 | ያለ ምንም ጥቅም ማበደር | ሁለት ጊዜ ሙስሊም ወንድሙን ያለ ምንም ጥቅም ያበደረ ሰው አንድ ጊዜ በነፃ እንደሰጠው ይቆጠራል፡፡ |
| 40 | ድህነት ያለበትን ባለ እዳ ሰው መታገስ (ማለፍ) | ሰዎችን የሚያበድር አንድ ሰው ነበርና ለሰራተኛው፡- የቸገረው ሰው ካጋጠመህ እለፈው፡፡ እሱን በማለፋችን አላህ ቢያልፈን፣ ብሎ ነበርና ከጌታው ጋር ተገናኘቶ አለፈው፡፡ |
| 41 | በጂሃድ ላይ ሁኖ አንዲት ቀን መፆም | በጂሃድ ላይ እያለ አንድ ቀን የፆመ ሰው አላህ ፊቱን ከእሳት የሰባ አመት መንገድ የሚያስኬድ ያህል ያርቅለታል፡፡ |
| 42 | በየወሩ ሶስት ቀንንና የዐረፋንና የዐሹራን ቀናት መፆም | በየወሩ ሶስት ቀኖችንና ረመዷንን ወር የፆመ ሰው እድሜውን ሙሉውን እንደፆመ ነው፡፡ (ስለ ዐረፋ ቀን ፆም ተጠይቀው ያለፈውንና የመጪውን አመት ወንጀል ያስምራል ብለዋል፡፡) ስለ ዐሹራእ ቀን ፆም ተጠይቀውም ያለፈውን አመት ወንጀል ያስምራል ብለዋል፡፡) |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| | ከሸዋል ስድስት ቀኖችን መፆም | ረመዷንን ፁሞ ከሸዋል ስድስት ቀንን የፆመ ሰው እድሜውን ልክ እንደ ፆመ ነው ብለዋል፡፡ |
| 44 | የተራዊህን ሶላት ኢማሙ እስከሚያበቃ ድረስ ከሱ ጋር አብሮ መስገድ | ኢማሙ እስከሚያበቃ ድረስ አብሮ የሰገደ ሰው ሌቱን ሙሉ ቁሞ እንዳደረ ሰው ይቆጠርለታል፡፡ |
| 45 | ትክክለኛ ሐጅ | ሐጅ አርጎ ጸያፍ ድርጊት ያልፈጸመ ሰው እናቱ በወለደችው ዕለት እንደነበረ ንፁህ ይሆናል፡፡ (ትክክለኛ ሐጅ ከጀነት በስተቀር ምንዳ የለውም፡፡) |
| 46 | በረመዷን ወር ዑምራን መፈፀም | በረመዷን ወር ዑምራ ማድረግ ሐጅ እንደማድረግ (ከእኔ ጋር ሐጅ እንደማድረግ) ይቆጠራል፡፡ |
| 47 | በመጀመሪያዎቹ የዙልሒጃ ወር አስርት ቀናት የሚሰራ መልካም ተግባር | ከእነዚህ አስር ቀኖች የበለጠ መልካም ስራዎች አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሚሆኑበት ቀን የለም፡፡ ጂሃድም ቢሆን፡፡ ያአላህ መልክተኛ ከነገንዘቡ ለጂሃድ ወጥቶ ምኑም ሳይመለስ የቀረ ካልሆነ በስተቀር ጂሃድም ቢሆን፡፡ ብለዋል፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| 48 | የኡድሂያ ዕርድ | ሱሃቦች ነቢዩ እኒህ ኡድሂያዎች ምንድን ናቸው ሲሏቸው የአባታችሁ የኢብራሂም ሱና ነው አሏቸው:: እኛ በእሷ ምን አለን ሲሏቸው በፀጉሯ ልክ ሐሰና አላችሁ አሏቸው:: በሱፉስ ምን አለን ያአላህ መልክተኛ ሲሏቸው በሱፋ ፀጉርም ልክ ሐሰና አላችሁ አሏቸው:: |
| 49 | የዓሊም (ዐዋቂ ሰው) ክብር እና ማዕረግ | አዋቂ ሰው ካለ እውቀት ዒባዳ ከሚያደርግ ሰው ላይ ያለው ብልጫ እኔ ከእናንተ መካከል አነስተኛ ከምትሉት ሰው ጋር ያለኝን ብልጫ ያህል ነው:: ከዚያም ነቢዩ (አላህ ፣መላይኮች፣ የሰማይና የምድር ባለቤቶች በዋሻዋ ውስጥ ያለች ጨጨጊን እንኳን ሳትቀር ሰዎችን ኸይር ለሚያስተምር ሰው ዱዓ ያደርጋሉ) ብለዋል:: |
| 50 | በአላህ ዲን ላይ መሰዋትን በትክክል መመኘት (አላህን መለመን) | በትክክል (በእውነት ከልቡ) በሸሀዳ መሞትን የተመኘ ሰው በቤቱ በፍራሽ ላይ እንኳን ቢሞት የሸሂድ ማእረግ ይሰጠዋል:: |
| 51 | አላህን ፈርቶ ማልቀስና ለአላህ ዲን ጥበቃ መቆም - በአሏህ ላይ መመካት፤ መተኮስን፤ ሩቅያ እንዲደረግለት ከመጠየቅ፤ ገድን መተው | ሁለት አይኖች እሳት አይነካቸውም:: እነሱም አላህን ፈርታ ያለቀሰች አይንና ለጅሃድ ዘብ ስትጠብቅ ያደረች አይን:: - አሏህ በመናም የቂያማ ቀን ዑመቶቼ የሚሆኑትን አሳየኝ፤ እነዚህ 70ሺ ሰዎች ያለምንም ሂሳብ ጀነት የሚገቡ ናቸው... |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| 52 | ትናንሽ ልጆች የሞቱበት ሰው | ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሶስት ልጆች የሞቱበት ሙስሊም አላህ ጀነት ያስገባዋል፡፡ |
| 53 | አይኑ ጠፍቶበት የታገሰ ሰው | አላህ፡- በሁለት ወዳጆቹ (አይኖቹ) የፈተንኩትና የታገሰ ባርያዬ በሁለቱ ምትክ ሁለት ጀነቶች እለውጠውአለሁ፤ ብሏል፡፡ |
| 54 | ለአላህ ብሎ አንድን ወንጀል የተወ ሰው | አንድን ነገር አላህን ፈርተህ አትተውም፣ በእሱ የተሻለን ነገር የለወጠህ ብትሆን እንጂ፡፡ |
| 55 | ምላስንና ብልትን መጠበቅ | በሁለት ፂሞችና በሁለት ጭኖቹ መካከል ያሉት አካሎችን ለመጠበቅ ዋስትና የገባልኝ ሰው እኔ ደግሞ ለጀነት ዋስ እሆነዋለሁ፡፡ ምላስንና ብልትን የጠበቀ ማለት ነው፡፡ |
| 56 | ወደ ቤት ሲገባም ሆነ በምግብ ጊዜ ቢስሚላህ ያለ ሰው | ወደቤቱ ሲገባና ሲመገብ አላህን ያወሳ ሰው ሰይጣን (ለባልንጀሮቹ)፡- ማደሪያም ሆነ እራት የላችሁም ይላል፡፡ ሲገባ አላህን ከላወሳ ደግሞ፡- ማደሪያ አግኚታችኋል ይላል፡፡ ሲመገብም አላህን ካላወሳ፡- እራትም አግኚታችኋል ይላል፡፡ |